# ሥርዓተ ልመት እና ቁስ አካል ፡ የሙከራ ጥያቄዎች

## ክፍል ሁለት

**መመሪያ፡ የሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ትክክል ከሆኑ እውነት ስህተት ከሆኑ ደግሞ ሐሰት በማለት መልሱ።**

1. የምግብ መፈጨት በተለያዩ የምግብ መፍጫ አካላት፣ ፈሳሾችና ኢንዛይሞች አማካይነት ይከናወናል።

2. በስርዓተ ልመት ውስጥ ምግብ የሚፈጭባቸው ዋና አካላት አፍ፣ ጨጓራና ትንሹ አንጀት ናቸው።

3. ከአፍ ወደ ጉሮሮ የደረሰው ምግብ ወደ ጨጓራ ለመድረስ ረጅም ጊዜ ይወስዳል።

4. ኢንዛይሞች የምግብ ልመት ሂደት እንዲፋጠን ያደርጋሉ።

5. ሃይድሮ ክሎሪክ አሲድ ደካማ አሲድ በመሆኑ ጀርሞችን መግደል አይችልም።

6. የሰረገው ምግብ ወደ ተለያዩ የአካል ክፍሎች የሚጓጓዘው በደም ሥሮች አማካይነት ነው።

7. በትልቁ አንጀት ውስጥ ከፍተኛ የሆነ የምግብ የመፍጨት ተግባር ይከናወናል።

8. ያልተፈጨ ምግብ ሁሉ ለተወሰነ ጊዜ በሬክተም (ፊንጢ) ውስጥ ይጠራቀማል።

9. ውሃ፣ ድንጋይ፣ ብረትና እንጨት የቁስ አካል ምሳሌዎች ናቸው።

10. ቁስ አካል ድብልቅ ያልሆኑ ልዩ ቁሶችና ድብልቅ ልዩ ቁሶች በመባል በሁለት ይመደባል።

11. ወርቅ፣ ብረት እና ውሃ የድብልቅ ልዩ ቁሶች ምሳሌዎች ናቸው።

12. ውህድ ማለት ሁለትና ከሁለት በላይ ከሆኑ ንጥረ ነገሮች በኬሚካዊ መስተጋብር የሚፈጠር ልዩ ቁስ ነው።

13. ካርቦን ዳይኦክሳይድ እና የገበታ ጨው የንጥረ ነገሮች ምሳሌዎች ናቸው።

14. ማግኒዚየም ሃይድሮክሳይድ እና ሶድየም ሃይድሮክሳይድ የተለመዱ የቤዞች ምሳሌዎች ናቸው።

15. ሶድየም ክሎራይድ (የገበታ ጨው) የጨው ዓይነት ውህድ ነው።

LIVEWORKSHEETS

መመሪያ፡ በ "ሀ" ረድፍ ስር ለተጠቀሱት ቃላት ወይም ሐረጎች ተስማሚ የሆኑትን ከ "ለ" ረድፍ ስር በመምረጥ ትክክለኛውን ቁጥር በባዶ ቦታው ላይ ሙሉ።

| ረድፍ "ሀ" | ረድፍ "ለ" |
|---|---|
| ............ አፍ፣ ጉሮሮ፣ ጨጓራ፣ ትንሹና ትልቁ አንጀት በጥቅሉ | 1. አግልሎት (Neutralization) |
| ............ አፍንና ጨጓራን የሚያገናኝ ቱቦ | 2. አፍ |
| ............ ምግብ መፈጨት የሚጀምርበት አካል | 3. ንጥረ ነገር |
| ............ ጀርሞችን ለመግደል ጨጓራ ውስጥ የሚገኝ ኃይለኛ ፈሳሽ | 4. የምግብ መተላለፊያ ቱቦዎች |
| ............ የምግብ ልመት የሚጠናቀቅበት አካል | 5. ትልቁ አንጀት |
| ............ በትንሹ አንጀት ግድግዳ ላይ ያሉ ጣት መሰል ነገሮች | 6. ጉሮሮ |
| ............ ምግብ የማይፈጭበት፣ ነገር ግን ውሃ የሚመጠጥበት አካል | 7. ሃይድሮ ክሎሪክ አሲድ |
| ............ ከአንድ ዓይነት አቶም ብቻ የተሠራ ልዩ ቁስ | 8. ውህድ |
| ............ በውስጣቸው ኦክስጅንና አንድ ሌላ ንጥረ ነገር ብቻ የያዙ | 9. ቪላይ |
| ............ በሁለትና ከዚያ በላይ ንጥረ ነገሮች መስተጋብር የሚፈጠር | 10. ኦክሳይዶች |
| ............ የአሲድና ቤዝ መፀገበር ሂደት | 11. ትንሹ አንጀት |
| ............ ሶድየም ሃይድሮክሳይድ እና ካልሲየም ሃይድሮክሳይድ | 12. ቤዞች |

LIVEWORKSHEETS